ምስክሮች የሰጡትን ቃል መነሻ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23879 ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31359 ታህሣሥ 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ቤቱን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 599 ሚያዝያ 18 ቀን 1996 ዓ.ም. ቤቱን በተመለተ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የተደረገውን እድሳት ምን ያሕል ገንዘብ እንዳስወጣና በመጀመሪያው ቤት ላይ ምን ያሕል የአይነትና የመጠን ለውጥ ያደረገ መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 መሠረት በልዩ አዋቂ በማስገመት የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 32147

መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ መሐመድ አብዲ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አብዱራሂም አብዲ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በውርስ የተላለፈልኝን መሬት ተከሣሽ በጊዜያዊነት እንዲገለገልበት ሰጥቼው ለመልቀቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ እንዲያስረክብ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቦታ የተከሣሽ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ በከሳሽ በኩል የቀረበው ክስ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አክራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ይግባኝ ባይ ክስ ባቀረበበት ቦታ ላይ መብት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃው የሚያረጋግጥ ስለሆነ መ/ሰጭ ለይግባኝ ባይ ሊመልስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታው ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በቅድሚያም ችሎቱ የተመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ዳኝነት የጠየቁት በውርስ የተላለፈላቸውን መሬት አመልካች በጊዜያዊነት እንዲገለገሉበት ሠጥተዋቸው ነገር ግን አመልካች መሬቱን ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው እንዲመልሱ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 6 መሠረት በከተማ ባለርስትና በከተማ ጭሰኛ መካከል ያለው ግንኙነት እንደፈረሰ ጭሰኛው ለከተማ ባለርስት ከሚከፍለው ኪራይና ሌላ ክፍያ እንደዚሁም ከማንኛውም አገልግሎትና ዕዳ ነፃ እንደሆነ ከመደንገጉም በላይ ማንኛውም ጭሰኛ በያዘው የከተማ ቦታ ላይ የይዞታ መብትም እንደማይኖረው ተመልክቷል፡፡

ለክሱ ምክንያት የሆነው መሬት በአዋጅ የመንግሥት መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ አመልካችን ለመክሰስ የማያበቃ መነሻ ምክንያት /Cause of action/ የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 231 ላይ እንደተመለከተውም ማንኛውም ፍ/ቤት የክስ አቤቱታ ሲቀርብለት ተከሣሽ የሆነው ወገን ክሱን እንዲከላከል ከመጥራቱ በፊት ከሳሹ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መነሻ ምክንያት ያለው ስለመሆኑና ፍ/ቤቱም አቤቱታውን ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ መመርመር ይኖርበታል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪ አመልካች ሊመልስልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ ያቀረበበት መሬት በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የመንግሥት ሀብት ስለሆነ ከመነሻው አቤቱታቸው የክስ ምክንያት እንደሌለው መገንዘብ ስለሚቻል የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ማለት ሲገባው አከራክሮ



ውሣኔ መስጠቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የጅጅጋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በሚያዝያ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ